# የሃዘን መግለጫ

ወንድማችን ኣቶ ሰይድ መሃመድ ባደረበት ህመም ምክንያት ሃኪም ቤት ገብቶ ሲታከም ከቀየ በኍላ እ.ኣ.ኣ ግንቦት 13 ቀን 2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶኣል።

ኣቶ ሰይድ እ.ኣ.ኣ በ1957ዓ.ም በወሎ ክፍለ ሃገር ተወልዶ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በደሴና ኣካባቢ ትምህርት ቤቶች ኣጠናቆ ኣል። እ.ኣ.ኣ1978 ዓ.ም ወደ ጀርመን ሃገር ከተሰደደ በኍላ ለረጅም ዓመታት በKobelenz ና በDarmstadt
ከ2004ዓ.ም ጀምሮ ኣስከኣረፈበት ቀን ድረስ በBerlin ከተሞች ኖሮኣል። በህይዎቱ ዘመናት በፀባዩ ቀናነትና በሞያዉ የሰዉ ልጅ ኣክባሪ ወገን ኣፍቃሪ ሃገርና ባህል ኣስከባሪ መሆኑን በቅርብ ለሚያዉቁት ወዳጆቱ ሁሉ ግልፅ ከመሆኑም በላ የሰኣሊነት ሞያዉና ስራዎቹ ታሪካዊ ምስክሩ ናቸዉ።
የኣቶ ሰይድ የቀብር ስነስርኣት እ.ኣ.ኣ ሰኞ ግንቦት 29.2006 ዓ.ም በ Berlin ከተማ  ከቀኑ በ11:00 ሰዓት ይፈፀማል። ኣስከሬኑ ከግንቦት 13.05.06 እስከ እለተቀብሩ ድረስ  ለዚህ ጉዳይ ባለሙያ ለሆኑ ድርጅቶች (Beerdigungsinstitute) ተሰጥቶ በልዩ የማቆያ ቦታ ታሽጎ ይቆያል።
በቀብሩ ስነስርኣት ላይ ለመገኘት የሚፈልጉ ወገኖች ካሉ ደርሶ መልስ ኣዉቶብስ ተከራይተን እሱን ለመሰናበት ኣስበናል። ለዚሁም የሰዉ ብዛት በቅድሚያ ቢታወቅ የኣዉቶብሱን ኣይነትና የመጕጕዟ ዋጋዉን ለማወቅ ይረዳናል። በቀብር ስነስርኣቱ ላይ ተገኝቶ እሱን ለመሰናበት የምትፈልጉ ሁሉ ይህ ማስታወቂያ የተለጠፉበት መገናኛ ቦታዎች ተዘጋጅቶ በሚገኘዉ ፎርም ላይ እንድትመዘገቡ ጥሪያችንን እንኣቀርባለን።
ሰይድ Berlin ከገባ በኍላ ብዙ ኢትዮጵያዉያንን ኤርትራዉያንን ጀርመኖችንና የተለያዩ የሙያ ሰዎችን ተዋዉቊል። ሆኖም ግን በችግሩ ቀናት በተለይም ታሞ እስከ ኣረፈበት ቀን ድረስ ከጎኑ ሆነዉ የሞራልና የቁሳቁስ እርዳታቸዉን ሲለግሱት የነበሩ ሁለት ኢትዮጵያዉያን ብቻ ናቸዉ። እነኝህ ግለሰቦች ጊዜያቸዉን ከቤተሰብሃላፊነትና ከእረፍት ሰኣታቸዉ ቀንሰዉ ሌሊት ተቀን ሰይድን ከማስታማማቸዉም በላይ ንብረታቸዉንም በመሰዋእት ታላቅ ኣስተዋፅኦ ኣድርገዋል። ዛሬም ሰይድ ካረፈበት ቀን እስከ እለተመቃብሩ ድረስ ለኣስከሬን ማቆያ ወጪ የሚሸፍኑት እነዚሁ ግለሰቦች ናቸዉ። ከቡራን በDarmstadt ና Farankfurt ኣካባቢ የምትኖሩ ኢትዮጵያዉያንና ኤርትራዉያን
"50 ሎሚ ለ50 ሰዉ ጌጡ ለኣንድ ሰዉ ግን ሸክሙ" እንደሚባለዉ ኣቶ ሰይድ መሃመድ ለሰጠን ክብርና ፍቅር ዉለታ መመለስ ባንችልም ለህሊናችን ስንል ፈቃደኞች የሆን ሁሉ የኣቅማችንን ያህል ገንዘብ ኣዋጥተን ከላይ የተጠቀሱትን ወዳጆቹን ተባብረን ወጪዎቸን ብንሸፍን  የመንፈስ እርካታ ይሰጠናል ብለን እናስባለን።
ሃሳባችንን የምትደግፉ ሁሉ ከዚህ በታች ስማቸዉና ስልካቸዉ ለተጠቀሱት ግለሰቦች ደዉላችሁ የበኩላችሁን ኣስተዋፅኦ ማድረግ እንደምትችሉ በትህትና እናስታዉቃለን።

| | |
|---|---|
| ወ/ሮ ሳራ ገብረ ወልድ | 01708157311 Darmstadt |
| ወ/ሮ ፀዳል ፀጋዬ | 06151 - 711674 Darmstadt |
| ኣቶ ሚካኤሌ ተሰፋዬ | 06151 - 717386 |
| ኣቶ ኃይሉ ሞገስ | 01772601227 o. 016151-8003931 Darmstadt |

ከማክበር ሰላምታ ጋር
ኣስተባባሪዎች